## መልእክት አራት

## ክርስቶስ በሂደት እንዳለፈው ሦስታንዱ አምላክ ማዕከል

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ማቴ. 28፥19፤ 1 ቆሮ. 15፥45፤ 2 ቆሮ. 3፥17፤ 13፥14

I. **የመለኮታዊው ሥላሴ ግልጹ መገለጥ ያለው በማቴዎስ 28፥19 ነው፦ "እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ወደ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም ውስጥ እያጠመቃችኋቸው፣ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (*ከሪካቨሪ ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስ በቀጥታ የተተረጎመ*)፡**

ሀ. "ወደ...ስም ውስጥ" የሚለው ማንነትን ያመለክታል፦

1. መጠመቅ ማለት (ማንነትን ወደ ሚያመለክተው) ወደ አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ ስም ውስጥ፣ በሂደት ካለፈው ሦስታንዱ አምላክ ጋር ወዳለ ሕይወታዊ ጥምረት ውስጥ መጠመቅ ነው።
2. በ 28፥19 ያለው *ወደ...ውስጥ* የሚለው በሮሜ 6፥3፤ በገላትያ 3፥27 እና በ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፥13 እንዳለው ጥምረትን ይጠቁማል።
3. ሰዎችን ወደ ሦስታንዱ አምላክ ስም ውስጥ ማጥመቅ፣ እነርሱን ከእርሱ ጋር ወዳለ መንፈሳዊና ምሥጢራዊ ጥምረት ውስጥ ማጥመቅ ነው።
4. በማቴዎስ 28፥19 ለሥላሴ አንድ ስም አለ፦

   ሀ. ስሙ ለማንነቱ የመለኮታዊ አቻ ጥቅል ድምር ነው።

   ለ. አማኞችን ወደ ሥላሴ ስም ውስጥ ማጥመቅ እነርሱን ሦስታንዱ አምላክ ወደሆነው ነገር ሁሉ ውስጥ ማጥመቅ ነው።

ለ. እግዚአብሔር ሦስት-በ-አንድ ነው—2 ቆሮ. 13፥14፦

1. በማቴዎስ 28፥19 ጌታ ስለ ሦስት ማንነቶች—ስለ አብ፣ ስለ ወልድ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ—ይናገራል።
2. እዚህ ጋር ስለ አብ፣ ስለ ወልድ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር፣ በመጀመሪያው ጽሑፍ *ስም* የሚለው በነጠላ ቁጥር ተቀምጧል።
3. ይህ ማለት አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ሦስት ናቸው፤ ስሙ ግን አንድ ነው።
4. ለሦስት ማንነቶች አንድ ስም መሆኑ በእውነቱ ምሥጢራዊ ነው፣ እግዚአብሔር ሦስት-በ-አንድ መሆኑንም ይገልጣል።
5. ይህ ስም ሦስቱንም—አብን፣ ወልድን እና መንፈስ ቅዱስን—ያካትታል፣ እግዚአብሔር ሦስት-በ-አንድ መሆኑም ይገልጣል።
6. ምንም እንኳ እግዚአብሔር ልዩና ብቸኛ በሆነ መንገድ አንድ ቢሆንም፣ ነገር ግን ሦስት ማንነቶች—አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ—አሉ።

II. **በክርስቶስ እንደሚያምኑ ሰዎች፣ በሂደት ወዳለፈው ሦስታንዱ አምላክ ውስጥ ተጠምቀናል፦**

ሀ. በማቴዎስ 28፥19 የተሰጠው ትእዛዝ ጌታ ኢየሱስ፣ በሂደት ያለፈው የሦስታንዱ አምላክ መጠናቀቅ ወደሆነው ወደ ትንሣኤ ውስጥ ከገባ በኋላ በእርሱ የተሰጠ ነበር።

ለ. ሦስታንዱ አምላክ በተሠግዎ በጀመረው፣ የሰብዕና ኑሮንና ስቅለትን ባካተተውና በትንሣኤ በተጠናቀቀው ሂደት አልፏል።

ሐ. የሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ የሆነው ክርስቶስ በትንሣኤ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ—1 ቆሮ. 15፥45፤ 2 ቆሮ. 3፥17።

መ. ይህ መንፈስ፣ አማኞች ወደ መለኮታዊው ሥላሴ ውስጥ ይጠመቁ ዘንድ የሦስታንዱ አምላክ መጠናቀቅ ነው።

ሠ. በአንድ በኩል፣ ማቴዎስ 28፥19 ስለ አብ፣ ስለ ወልድ እና ስለ መንፈስ ቅዱስ ይናገራል፤ በሌላ በኩል፣ በዚህ ጥቅስ ውስጥ አንድ ስም ብቻ አለ—የአብ፣ የወልድ እና የመንፈስ ቅዱስ ስም።

ረ. ወደ ሥላሴ ማንነት ውስጥ መጠመቅ በሂደት ያለፈው የሦስታንዱ አምላክ ከፍተኛ እና የመጨረሻ መጠናቀቅ በሆነው ሁሉን ባካተተው፣ በተጠናቀቀው መንፈስ መጠመቅ ነው፦

1. ይህ ማለት ወደ አብ ብልጥግናዎች ውስጥ፣ ወደ ወልድ ብልጥግናዎች ውስጥና ወደ መንፈስ ብልጥግናዎች ውስጥ መጠመቅ ነው።
2. እንደተጠመቁ ሰዎች፣ አሁን ከሦስታንዱ አምላክ ጋር በሕይወታዊ ጥምረት ውስጥ ነን፤ ስለዚህ፣ አብ ያለው ሁሉ፣ ወልድ ያለው ሁሉ እና መንፈስ ያለው ሁሉ የእኛ ሆኗል።

ሰ. ወደ ሦስታንዱ አምላክ ስም ውስጥ መጠመቅ ከእርሱ ጋር ወዳለ ወደ ምሥጢራዊ ጥምረት ውስጥ መጨመር እና እግዚአብሔር የሆነውን ሁሉ ወደ ማንነታችን ውስጥ መውሰድ ነው።

**III. ክርስቶስ በሂደት ያለፈው የሦስታንዱ አምላክ ማዕከል ነው—2 ቆሮ. 13፥14፡-**

*ሀ. በሂዳት ያለፈው* የሚለው ሦስታንዱ አምላክ ያለፈባቸውን ወሳኝ እርምጃዎች ያመለክታል፡-

1. ከተሠግዎው በፊት እግዚአብሔር መለኮታዊው ባሕርይ እንጂ የሰብዕና ባሕርይ ስላልነበረው በሂደት ያላለፈ ነበር፤ ነገር ግን በተሠግዎ፣ በሰብዕና ኑሮ፣ በስቅለት፣ በትንሣኤ እና በዕርገት፣ ሦስታንዱ አምላክ በሂደት አልፏል፣ ተጠናቆማል።
2. በራእይ፣ ሦስታንዱ አምላክ መለኮትነት፣ ሰብዕና፣ የሰብዕና ኑሮ፣ ሁሉን-ያካተተ ሞት፣ ኃይለኛው ትንሣኤ እና ሁሉን ጥሶ የሚወጣው ዕርገት ያለው በሂደት ያለፈውና የተጠናቀቀው ነው—1፥4-5።

ለ. በሂደት ያለፈውና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ መንፈስ ነው—22፥17፤ ዮሐ. 7፥39፡-

1. መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ ሲያሜዎች ንጥረ ነገሮች ሁሉ ጥቅል ድምር ነው—ማቴ. 3፥16፤ 10፥20፤ ሉቃ. 1፥35፤ 4፥18፤ ሮሜ 8፥9፤ ገላ. 4፥6።
2. በሂደት እንዳለፈውና እንደተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ መጠናቀቅ፣ መንፈስ የእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ በረከት ነው—ገላ. 3፡14።

ሐ. በራእይ መጽሐፍ ያለው ሦስታንዱ አምላክ የሚገናባውና የተገነባው አምላክ ነው—21፥18-19፣ 21፡-

1. መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠናቀቀው በመጀመሪያ የነበረውን እግዚአብሔርን ራሱ በሆነችው በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ነው—ዘፍ. 1፥1፤ ራእ. 21፥10፡-
   - ሀ. ልዩና ብቸኛው አምላክ በስተመጨረሻ ለዘላለማዊው መገለጡ ከተማ ወደ መሆን ይተልቃል፣ ይስፋፋልም።
   - ለ. በኢኮኖሚው እግዚአብሔር አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ሆኗል—ቁ. 10።
   - ሐ. በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ሦስታንዱ አምላክ ወደ ዋጃቸው ሰዎች ውስጥ ተሠርቷል—ቁ. 18-19፣ 21።
2. አዲሲቱን ኢየሩሳሌም የሆነው ሦስታንዱ አምላክ የሚገነባውና የተገነባው አምላክ ሆኗል—2 ሳሙ. 7፥12፣ 14፤ ማቴ. 16፥18፤ ኤፌ. 3፥17፡-
   - ሀ. በሂደት ያለፈውና የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ እንደ ምንጭ፣ እንደ ንጥረ ነገር እና እንደ ውስጠ ነገር ራሱን ወደ ማንነታችን ውስጥ በመገንባት ቤተ ክርስቲያንን እየገነባ ነው—ቁ. 17።
   - ለ. እግዚአብሔር በክርስቶስ ራሱን ወደ ማንነታችን ውስጥ መገንባትና እኛን ወደ ማንነቱ ውስጥ መገንባት የሆነውን መሻቱን እየፈጸመ ነው፤ በስተመጨረሻ፣ የዚህ ግንባታ ውጤት አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ትሆናለች—ራእ. 21፥2፣ 10።

መ. በራእይ መጽሐፍ፣ ለመለኮታዊ እደላ የሆነው የመለኮታዊው ሥላሴ የተጠናቀቀ መገለጥ አለን—22፥1-2፤ 7፥17፤ 21፥6፤ ዮሐ. 4፥14፡-

1. መለኮታዊው እደላ እንደ ሕይወታቸው፣ እንደ የሕይወት አቅርቦታቸው እና እንደ ሁሉ ነገራቸው እግዚአብሔር ወደ መረጣቸው እና ወደ ዋጃቸው ሕዝቡ ውስጥ ራሱን ማስተላለፉ ነው—2 ቆሮ. 13፥14።
2. በመለኮታዊው እደላ ውስጥ አብ ምንጭ ነው፣ ወልድ ፍልቅ ነው፣ መንፈስ ፍሰት ነው።

*© 2025 Living Stream Ministry*